Amharric

# ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ



እርግዝናን ለመከላከል ጊዜ አለዎ አሁንም ይደርሳሉ

## ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ አገልግሎቱ ለድንገተኛ ሁኔታ ብቻ ነው

ለብዙ ሴቶች ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ክኒን ለድንገተኛ ሁኔታ እንጂ ለዘውትር የሚወሰድ መከላከያ ሊሆን አይችልም። እንደዘውትር የወሊድ መከላከያ አስተማማኝ ካለመሆኑም በላይ፤ ዋጋው ሊወደድ ይችላል።

የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽሙ ከሆነ የዘውትር የወሊድ መከላከያ በሆኑት እንደክኒን፣ መርፌና፣ኮንዶም (ላስቲክ) በመሳሰሉት ይጠቀሙ።

ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚተላለፉ በሽታዎች ወይም ኤድስን ሊከላከልልዎት አይችልም። ኮንዶም (ላስቲክ) በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚተላለፉ እንደኤድስ ካሉ በሽታዎች ለመከላከል ያለው ኃይል ከፍተኛ ነው።

## ጉዳት ያመጣል ብለው ያስባሉን?

የአሜሪካ የምግብና የመድኃኔት አስተዳደር ክፍል (ዩ.ኤስ. ፋድ ኤንድ ድራግ አድሚኒስትረሽን) ጉዳት አያመጣም የሚል መግለጫ ሰጥቷል። የወሊድ መከላከያ ሳይጠቁሙ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከተፈጸመ እርግዝናን በመከላከል ያለው ኃይል ከፍ ያለ ነው።

## ያልታሰበ የጤና ጉዳት ሊያመጣ ይችላልን?

እንዳንድ ሴቶች ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ሲወስዱ የማቅለሽለሽ፣ የማስታወክ፣ የራስ ምታት፣ ወይም የጡት መቁሰል ስሜት ሊሰማቸው ይችላል። እንደዚህ የሚሰማቸው ለአንድ ቀን ብቻ ነው። ከፕሮጀስትሮን ብቻ የተሠራ ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ክኒን አንዳንድ ያልታሰቡ የጤና ጉዳቶችን ሊያስከትል ይችላል። በተጨማሪም ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ የወር አበባዎን በጥቂት ቀናት ሊያስቀድመው ወይም ሊያዘገየው ይችላል።

## ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ እንዴት ላገኝ እችላለሁ?

የድንገተኛ የወሊድ መከላከያ መግዣ ፈቃድ ከሐኪምዎ ወይም ከጤና ክሊኒክ ማግኘት ይችላሉ። በአንዳንድ ቦታዎች በቀጥታ መድኃኔት ቤት በመሄድ ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ መግዛት ይቻላል። በየአገሩ ለሚገኙ የድንገተኛ የወሊድ መከላከያ እና እንደድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ሊያገለግሉ የሚችሉ የዘውትር የወሊድ መከላከያ ዓይነቶች የሚከተለውን ድረ ገጽ ይመልከቱ፦

**http://www.not-2-late.com**

(በእንግሊዘኛ፣ በስፓንሽ፣ በፈረንሳይኛ፣ በዓረበኛ ማንበብ ይችላሉ።)

**1-888-668-2528**

**(1-888-NOT-2-LATE)**

PATH
A catalyst for global health

ፓዝ ዓለማቀፋዊ የበጎ አድራጊ ድርጅት የዓለም ጤናን ለማሻሻል ይጥራል። ከግልና ከሕዝብ ተቋሞች ጋር በመተባበር፤ ፓዝ ለየቦታው ተስማሚ የሆኑ ስሉጥ ቴክኖሎጂዎችን በመፍጠር፤ ዘለቄታዊና እንደየባሕሉ ተስማሚነት ያላቸውን የሕዝብ የጤና መፍትሔዎችን ያዘጋጃል። ለተጨማሪ መረጃ ድረ ገጽ፦ www.path.orgይጐብኙ።

## እርጉዝ ነኝ ብለው ይሰጋሉ?

ባለፉት አምስት ቀናት ውስጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አድርገው ከሆነና፤

- በወሊድ መከላከያ ሳይጠቀሙ ቀርተው ከሆነ፤
- ኮንዶሙ (ላስቲኩ) ተቀዶ ከነበረ፤
- የወሊድ መከላከያ መርፌ መወግያዎ ጊዜ ዘግይቶ ከነበር፤
- በመደዳ ሁለት ቀን ወይም ከዛ በላይ የወሊድ መከላከያ ክኒን ሳይውዱ ቀርተው ወይም ዘግይተው ከጀመሩ፤
- የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተፈጸመብዎ በግዴታ ከሆነ፤

ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ክኒን መጠቀም ይችላሉ።

ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት በኋላ እርግዝናን ለመከላከል የሚጠቅም ዘዴ ነው። በአስቸኳይ ወይም በድንገተኛ ሁኔታ እርግዝናን ለመከላከል የሚጠቅሙ ሁለት የታወቁ መንገዶች አሉ፦

1. ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ክኒን (ወይም ኢመርጀንሲ ኮንትራሴፐቲብ ፒልስ 'ኢ.ሲ.ፒ.' ሌላ ስሙ ሞርኒንግ አፍተር ፒልስ) የግብረ ሥጋ ግንኙነት በተፈጸመ በአምስት ቀናት ውስጥ የሚወሰድ ክኒን፤ ወይም

2. አ.ዩ.ዲ. የሚባለው ማህጸን ውስጥ የሚቀመጥ የወሊድ መከላከያ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በተፈጸመ በሰባት ቀናት ውስጥ ሊደረግ ይችላል። ለተጨማሪ መረጃ ሐኪምዎን ያማክሩ።



**http://www.not-2-late.com**

(በእንግሊዘኛ፣ በስፓንሽ፣ በፈረንሳይኛ፣ በዓረበኛ ማንበብ ይችላሉ።)

## ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ክኒን (ኢ.ሲ.ፒ.) ምንድነው?

ኢ.ሲ.ፒ. የተባለው ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ዘውትር የምንጠቀምበት የወሊድ መከላከያ ክኒን ዓይነት ነው። የግብረ ሥጋ ግንኙነት በተፈጸመ በአምስት ቀናት ውስጥ መጠኑ ተስተካክሎ ከተወሰደ እርግዝናን ይከላከል። ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ክኒን ሁለት ዓይነት ነው።

- ፕሮጄስትሮን ከተባለ አካላዊ ቅመም ብቻ የተሠራ ክኒን የእርግዝናዉን እድል ከመቶ 89 እጅ ይቀንሰዋል።

- ኤስትሮጅን እና ፕሮጄስትሮን ከተባሉ አካላዊ ቅመሞች የተሠራ ክኒን የእርግዝናዉን እድል ከመቶ 75 እጅ ይቀንሰዋል።

መጠናቸው ተስተካክሎ ከተሰጠ፤ አንዳንድ የዘውትር የወሊድ መከላከያ የክኒን ዓይነቶች እንደ ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ሊያገለግሉ ይችላሉ። የወሊድ መከላከያ ክኒን በተለያየ መልኩ ስለሚዘጋጅ፤ አወሳሰዱም እንደአሠራሩ ይለያያል። ይህ ድረ ገጽ የየአገሩን የወሊድ መከላከያ ዓይነትና ትክክለኛ አወሳሰድ ይዘረዝራል፦http://www.not-2-late.com.

## ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ክኒን እንዴት መውሰድ እችላለሁ?

- ፕሮጄስትሮን ከተባለ አካላዊ ቅመም ብቻ የተሠራ ክኒን በአንድ ወይም በሁለት ጊዜ ሊወሰዱ ይችላሉ። ያለየወሊድ መከላከያ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በፈጸሙ በ120 ሰዓታት ውስጥ የመጀመርያውን ክኒን፤ የሁለተኛውን ክኒን ደግሞ የመጀመርያውን ከወሰዱ ከ12 ሰዓታት በኋላ ይውሰዱ።
- ኤስትሮጂን እና ፕሮጄስትሮን ከተባሉ አካላዊ ቅመሞች የተሠራ ክኒን በሁለት ጊዜ መወሰድ አለበት፦ የመጀመርያውን ክኒን በ120 ሰዓታት ውስጥ፤ የሁለተኛውን ክኒን የመጀመርያውን ከወሰዱ ከ12 ሰዓታት በኋላ ይውሰዱ።
- ሐኪምዎ ያዘዘልዎትን ወይም ከሁለቱ እርስዎ የሚስማማዎትን ዓይነት ክኒን ይውሰዱ።

## አይዘግዩ!



እርግዝናን ለመከላከል የግብረ ሥጋ ግንኙነት በፈጸሙ በአምስት ቀናት (120 ሰዓታት) ውስጥ ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ክኒን ይውሰዱ። ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ክኒን በደንብ የሚሠራው የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደተፈጸመ ወድያው በፍጥነት ከተወሰደ ነው።

## ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ክኒን እንዴት ነው የሚሠራው?

የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፤ ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ክኒን እርግዝናን የሚከላከለው ለተወሰነ ጊዜ ማህፅን ውስጥ እንቁላል እንዳይሰፍር በመከላከል ወይም በማዘግየት እንቁላል እንዳያኮርት በማድረግ ነው።

ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ክኒን ከእርግዝና በኋላ አይጠቅምም። ጽንስን ለማስወረድ የሚወሰድ ክኒንም አይደለም።

አሜሪካን አገር ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ በዚህ የድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ስልክ ቁጥር ይደውሉ። ለመደውል በነፃ ነው፤ ምሥጢርዎ ይጠበቅልዎታል፤ የ24 ሰዓት አገልግሎት ያገኛሉ።



**1-888-668-2528**

**(1-888-NOT-2-LATE)**